# ስድስተኛው የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን

# የአርብቶአደር ተወካዮች የጋራ አቋም መግለጫ

*(ጥር 16 ቀን 1996 ዓ.ም ያቤሎ ወረዳ፣ ዲደጡዩራ የአርብቶአደር መንደር)*

## ሀ. መግቢያ

1. የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች በቀደምት ዘመናት ትኩረት ተነፍገው፤ የኑሮ ዘይቤ እና ስልተ ምርት የሆነው አርብቶአደርነት ተንቆና ተገፍቶ በመቆየቱ አርብቶአደሮች ለከፋ ድህነትና ተደጋጋሚ ረሃብ ሰለባ ሆነው በመቆየታቸው፤
2. የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች በአምስት ብሔራዊ ፌዴራላዊ ክልሎች ከ120 በላይ ወረዳዎች መያዛቸው ፤ 42% የእንስሳት ሀብት፤ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት እና የነባር እውቀቶች ባለቤት መሆናቸው፣አርብቶአደርነት የሚሊዮኖች ዜጎች የሥራ መስክ እና በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከግምት ሳይገባ በመቅረቱ፤
3. አርብቶ አደርነት በውሳኔ ሰጭ አካላት ዘንድ በአግባቡ ባለመታወቁና እውቀቱ ባለመዳበሩ የተነሣ አርብቶአደሮች በሀገሪቱ የልማት ፖሊሲ ተሣታፊና ተጠቃሚ ሳይሆኑ መቆየታቸው ፤
4. ከላይ ከተራ ቁጥር 1-3 የተዘረዘሩት አብይ የአመለካከት እና የፖሊሲ ችግሮችን ለማስወገድ፣ አርብቶአደሮች ድምፃቸው ከፍ ብሎ የሚሰማበት እና ህልውናቸውን የሚነካ ማናቸውም ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞች ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆናቸው የሚንፀባረቅበት እና የሚፈተሽበት የጋራ መድረክ በማስፈለጉ፤
5. መንግስት፣ አርብቶአደሩ ህብረተሰብ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ እና ለጋሽ ድርጅቶች የሚያከናውኑት መልካም ስራዎች የሚደነቁበት፣ ልምድ የሚቀሰምበት፣ የባህል ልውውጥ እና የእርስ በእርስ ትውውቅና ወንድማማችነት የሚረጋገጥበት ሁነኛ መድረክ የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን እንዲሆን በ 1988 ዓ.ም በአርብቶአደሮች ጥያቄ በተወሰነው መሰረት ከ1991ዓ.ም ጀምሮ በአርብቶአደሮች፣ በሲቪል ማህበረሰቡ፣ በክልል መንግስታት እና በአንዳንድ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች በጋራ ሲከበር መቆየቱ፤
6. የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን ለስድስተኛ ጊዜ ሲከበር ዝግጅቱን በበላይ ሲመራ የቆየው ኮሚቴ ማለትም የፓርላማ የአርብቶአደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የአርብቶአደር አካባቢ ልማት መምሪያ እና ፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያ አባል የሆኑበት የበዓሉን የወደፊት ሁኔታ እንዲወስን በተሰጠው ሃላፊነት እና የአርብቶአደሮቹን የጋራ መግለጫ አግባብ ላለው ውሳኔ ሰጭ አካል በማቅረብ አስፈላጊው ይፈፀም ዘንድ በጋራ በተወሰነው መሰረት፤
7. ይህ የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች የአቋም መግለጫ በኮሚቴው እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል።

## ለ. የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን ታሪካዊ አመጣጥ

የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን በዓል መከበር የጀመረው ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ነው። በቦረና እና በፈልቱ አካባቢዎች የሚኖሩ አርብቶአደሮች በ1988 ዓ.ም ባቀረቡት ሀሳብ እና በኋላም በፓስቶራሊስት ኮንሰርን አሶሴሽን ኢትዮጵያ (PCAE) በተባለ አገር በቀል ግብረ ሰናይ ድርጅት ወደ ተግባር ተሸጋገሮ በዚህ ዓመት ለ6ኛ ጊዜ ተከብሯል። PCAE የመጀመሪያዎቹን ሶስት በዓላት ከአርብቶአደሮች እና አጋሮቻቸው ጋር ሲያስተባብር ቆይቶ ከ1994ዓ.ም ጀምሮ ፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያ የበዓሉን ዝግጅት በኃላፊነት በመረከብ ከክልል መንግስታት እና ከአንዳንድ የፌደራል መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ሲያዘጋጅ ቆይቷል።

የአርብቶአደር ቀን በአፍሪካ ደረጃ ብቸኛው እና ብርቅዬ ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ አንድናቆትን እያተረፈና የሚያስተናግዳቸው የአርብቶአደር ጉዳዮች ከፍተኛ ግምት በማግኘት ላይ ናቸው፡፡ የበአሉም ተሳታፊዎች በአይነት፣በደረጃና በቁጥር ጨምሯል፡፡

## ሐ. ስድስተኛው የአርብቶአደሮች ቀን አከባበር ሁኔታ

ይህ የዘንድሮ በዓል *የመሬት አጠቃቀም መብት ለአርብቶ አደሩ ዘላቂ ልማት* በሚል መሪ መፈክር በፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያ፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት (የአርብቶአደር ልማት ኮሚሽን) እና በአርብቶአደሩ ተወካዮች በጋራ አስተባባሪነት በጥር 16 ቀን 1996 ዓ.ም በያቤሎ ወረዳ ልዩ ስሙ ዲደጡዩራ በተባለ የአርብቶአደር መንደር ተከበረ፡፡ በዓሉም ከ2500 የሚልቁ አርብቶአደሮች፣ ከ200 በላይ የሆኑ እንግዶች፤ ከፍተኛ የፌደራል እና የክልል መንግስታት ባለስልጣናት፣የእንግሊዘና የኬንያ የፓርላማ ተወካዮች፤ ለጋሽ ድርጅቶች ፣ የተለያዩ የአርብቶአደሮች አካባቢ ተወካዮች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች ተወካዮች ፣ ተመራማሪዎች እና የዩኒቨርስቲ ተወካዮች ተሳታፊ ሆኗል፡፡

ከዋናው በዓል ቀን ቀደም ብሎ በአርብቶአደሮች የተመራ የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህ ፓናል ውይይት መጨረሻ የጋራ መግለጫ በማውጣት መግለጫውም በበዓሉ ላይ እንዲገለፅ በማለት ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም ከበዓሉ አንድ ሳምንት በፊት በፓርላማ የአርብቶአደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት እና በመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች መካከል የአርብቶአደሩን የመሬት አጠቃቀም መብት ፣ የድርቅ ሁኔታ እና ተቋማዊ አደረጃጀት ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

## መ. የጋራ አቋም መግለጫ

እኛ የሶማሌ፣ የአፋር፣ የኦሮሚያ እና የደቡብ ህዝቦች አርብቶአደር ተወካዮች በጥር 16 ቀን 1996 ዓ.ም በተከበረው በዓላችን የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡ የሚመለከተው አካል ይህንን ውሳኔያችንን ተቀብሎ ወደ ተግባር እንደሚለወጥልን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ የአቋም መግለጫው እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

1. ሁለንተናዊ የአርብቶአደሩን ጉዳዮች የሚከታተልና የሚያስፈፅም የመንግስት ተቋም በየደረጃው እንዲቋቋም፤
2. በአርብቶአደሩ አካባቢ የሚከሰቱ ግጭቶች በባህላዊ መንገድ መፍትሄ ለመስጠት እንዲያስችል በተለያዩ ጉዳዮች አርብቶአደሩን በመወከል ከመንግስት ጋር በመተባበር የሚሰሩ የአርብቶአደር ሽማግሌዎች ምክር ቤት በየደረጃው እንዲቋቋም፤
3. የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ በአርብቶአደሩ ተሳትፎ ተነድፎ እንዲተገበር፤
4. የመሰረታዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች በአርብቶአደሩ አካባቢ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፤
5. የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ቀን በመንግስት ዕውቅና እንዲያገኝ እና በብሄራዊ ቀናት ካላንደር ውስጥ እንዲካተት፤
6. አርብቶአደር እንስሳቱን በዋስትናነት በመጠቀም ከባንክ ብድር የሚያገኝበትን ሁኔታ እንዲመቻች፤
7. የሚቀጥለው የአርብቶአደሮች ቀን በፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያ፣ በፓርላማ የአርብቶአደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በትብብር ይዘጋጃል፡፡